**ሳምንታዊ ዜና (ሚያዝያ 16 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ መሬት ተቆርሶ ለሱዳን መሰጠቱን አመነ፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን ከጎንደር ታፍሰው ተወስደው ሱዳን ውስጥ እየተሰቃዩ አንድም የታሰረ የለም ሲል ገለጸ፣ ጦሩ በሱዳን ጉዳይ ማብራሪያ ይሰጠን ሲል ጥያቄ አቀረበ፣ ወያኔ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኪሣራ ውስጥ መዘፈቁ ተጋለጠ፣ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ የለኝም ሲል ነጋዴዎችን አባረረ፣ ንግድ ባንክም የሀገር ውስጥ ብር የለም እያለ ደንበኞቹን መለሰ፣ ምርኮኛው ኩማ ደመቅሳ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆኖ ተሾመ፣ የገቢዎች ሚኒስተር ፈረሰ፣ የሠራተኞቹ እጣ ፈንታ አደጋ ላይ ነው »»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ .....**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለሱዳን መስጠቱን አመነ:: መለስ ይህንን የገለፀው ረቡዕ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተወካዮች ምክር ቤት አባሎች አነሱት ለተባለው ጥያቄ ምላሽ በሰጠበት ወቅት መሆኑ ታውቋል::

በዚሁ ምላሽ ሰጠ በተባለበት ወቅት እንዳለው በአፄ ምኒልክ እና በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ እንደተፈረመውና በደርግ እንደተረጋገጠው ሁሉ የጎይን መስመርን ተከትሎ በኛም በኩል የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንቅስቃሴ ጀምረን የነበረ ቢሆንም በ1988 ዓ.ም ከሙባረክ ግድያ መኩራ ጋር በተያያዘ ድርድሩ ሊቋረጥ ችሎዋል ያለው መለስ በወቅቱ የሁለቱም ሀገራት ወታደሮች በድንበሩ ላይ ሰፈረው የቆዩ ሲሆን፣ከተወሰነ ቆይታ በሁዋላ የሱዳን ጦር ቦታውን ሲለቅ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንደገቡና በዚያው እንደቀሩ ገልጿል::

የወያኔው መሪ የሱዳን ጠቅላይ ሚኒስትር እስኪመስል ድረስ ለሱዳን ጥብቅና ቆሞ ሲወተውት የዋለ ከመሆኑም በላይ«የሱዳን ኢንቨስተሮች በ1988 ዓ.ም ቦታውን ለቀው ሲወጡ ኢትዮጵያውያኖች የሰፈሩበት በመሆኑ አሁን እነዚህ ኢንቨስተሮች ተመልሰው ወደ ቦታቸው መግባት አለባቸው» በማለት መሬት ቆርሶ የሰጣቸው መሆኑን በዚሁ በሰጠው ምላሹ ላይ እራሱን አጋልጧል::

አንዴ ከሱዳን ጋር የድንበር ማካለል አልተደረገም ሌላ ጊዜ ደግሞ በአፄ ሚኒልክ ስርዓት ወቅት የእንግሊዝ መኮንን በነበረው ቫለቃ ጉይን በተባለ መኮንን ድንበሩ የተከለለ ነው እያለ መላው ጠፍቶበት ሲዘላብድ የዋለው መለስ ዜናዊ በአጭሩ ግን መሬት ለሱዳን መሰጠቱን አምኗል::

በአካባቢው የተፈናቀለ ወይም የሚፈናቀል አንድም ኢትዮጵያዊ የለም ሲል የዋሸው የወያኔው መሪ መለስ በአሁን ሰዓት ከቦታው ላይ ታፈሰው ሱዳን ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ ታስረው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በቂ ማስረጃ መሆኑን የሀገሪቱ ዜጐች እየገለፁ ይገኛሉ::

በ1988 ዓ.ም የሱዳን ጦር ድንበሩን ለቅቆ ሲሄድ የሱዳን ኢንቨስተሮችም አካባቢውን ለቅቀው በመውጣታቸው ኢትዮጵያውያን ቦታውን ይዘው ሲጠቀሙበት ነበር ያለው መለስ ዜናዊ አሁን ግን ለተወሰደባቸው የሱዳን ኢንቨስተሮች ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሸጠበትን ቀብድ ላለመመለስ የሚያደርገው ከንቱ ሙከራ ነው ያሉት የሀገሪቱ ዜጐች በሊዝ ለውጭ ዜጐች መሬቱን ቸብችቦ ዛሬ መልሶ የሱዳን ነው እያለ ለሱዳኖች ጥብቅና መቆሙ በእጅጉ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉም ዜጐች በንዴት ይገልፃሉ፡፡

ከወያኔ ጋር በሊዝ ተፈራርመው በዚሁ ቦታ ላይ የልማት ሥራ እየሰሩ የሚገኙትን ኢትዮጵያዊ ባለሀብቶች የሱዳን ወታደሮች አፍሰው ወስደው ሱዳን ውስጥ አስረዋቸው እንደሚገኙ መለስ ዜናዊ ቢያውቅም አይኔን ግንባር ያድርገው ብሎ ያለ አንዳች ይሉኝታና ሐፍረት የታሰረ ዜጋ የለም እያለ ምላሽ መስጠቱ በሱዳን መንግስት ሳይቀር ትዝብት ላይ እንደሚወድቅ የሀገሪቱ ዜጐች በአግራሞት እየገለፁ ናቸው፡፡

በ1907 ዓ.ም አፄ ምኒልክ በወቅቱ የኬንያና የሱዳን ቀኝ ገዥ ከሆኑት እንግሊዞች ጋር ስምምነት ተፈራርመው ከሁለት ዓመት በሁዋላ በ1909 ዓ.ም በሻለቃ ጉይን በተባለው እንግሊዛዊ የድንበር ማካለሉ ሂደት ተከናውኖል ሲል የገለፀው መለስ በአፄ ኃይለ ሥላሴም ይሄው ውል እንደፀደቀና በደርግም ስርዓት እንዲረጋገጥ ተደርጓል ብሎ ምንም የታሪክ እውቀት ሳይኖረው ስለ ሸጠው መሬት ሲፈተፍት መደመጡ ያናድዳል ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ምሁር ዛሬ እሱ መሣሪያ በእጁ ስላለው ያሻውን ማለት ይችላል፡፡ ለ17 ዓመታት ምን እየፈፀመ እንደመጣ ሁላችንም የምናውቀው በመሆኑ አሁን ድርቅ ያለ ውሸት ቢናገርም ሊገርመን አይገባም ሲሉ ገልፀዋል፡፡

አያይዘውም የሚያሳዝነው ግን ለሀገር ድንበርና ለወገን ቅንጣት ታክል የመቆርቆር ስሜት ውስጡ እንደሌለ ከተረዳሁ የቆየሁ ቢሆንም ዛሬ ግን በጣም ተገንዝቤያለሁ ምላሽ ሲሰጥ በአማርኛ ተናገረ እንጂ የሱዳን ፕሬዝዳንት አልበሺር እንኳዋን ስለ ሱዳን ይሄንን ያክል ይዞ ሲከራከር አይደመጥም የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ግን በሚያሳዝንና በሚያስገርም ሁኔታ አቋዋም ይዞ ለሱዳን ቆሞ መከራከሩና የታሰሩ ኢትዮጵያውያኖች የሉም ማለቱ በጣም ያሳዝናል አንጀትም ያደብናል ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ገልፀዋል፡፡

ከኢትዮጵያ ለም መሬት ላይ 61 ኪሎ ሜትር ቆርሶ በነዳጅና በብር የለወጠው ወያኔ የጎንደር ሕዝብ ወደ አመጽ መግባቱን ሲረዳ ሠራዊት በቦታው ላይ አስፍሮ ሕዝቡን ከአካባቢው ያስለቀቀ መሆኑን ከስፍራው የሚወጡ

ዘገባዎች እያጋለጡ ባለበት በዚህ ወቅት መለስ የወሰድነውን መሬት ነው የሰጠናቸው ብሎ ያለ አንዳች ፍርሃት መግለፁ በእጅጉ አሳዛኝ ነው ያሉት አንድ አዛውንት እስከ መቼስ ነው እንዲህ ያለ የውሸት ድሪቶ ተሸክመን የምንጓዘው? ሲሉም በቁጭትና በእልህ ይጠይቃሉ፡፡

የድንበር መከላከል አልተረደገም፣ ቢደረግም አንድም አትዮጵያዊ አይፈናቀልም እያለ በሚለፍፍበት ወቅት እንኩዋን ሳይቀር በሱዳን ወታደሮች በርካታ የጐንደር ገበሬዎች እትብታቸው ከተቀረበበት ቀዬ ተነቅለው እየወጡ ሲሆን፣ የተቀሩትም ቢሆን ከብቶቻቸውን ሳር እንዳያስግጡና ውሃ ከወንዝ ቀድተው እንዳይጠቀሙ በማድረጋቸው ሕዝቡ እየተሰቃየ መሆኑን መለስ ዜናዊ እያወቀ መልሶ ለሱዳን ጥብቅና ቆሞ መከራከሩ በእጅጉ አሳፋሪና አሳዛኝ ታሪክ ነው ሲሉም እኚሁ አዛውንት ገልፀዋል፡፡

ወትሮም ከፋፋይና አስገንጣይ የሆነው የወያኔው መሪ ቢክድም በርካታ ኢትዮጵያውያን በሱዳን እስር ቤት ታጉረው የሚገኙ መሆኑንም ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይሄው የኢትዮጵያን መሬት ተቆርሶ ለሱዳን መሰጠቱን ተከትሎ በጦሩ ውስጥ ጥያቄ የተነሳ ሲሆን፤የወያኔ ጥቅመኛ ጀኔራሎች የጦሩን ጥያቄ ለማዳፈን ቢሞክሩም ነገሩ እየተባባሰ በመሄዱ መለስ ዜናዊ ስዩም መስፍንን ወደ ሱዳኑ ፕሬዝዳንት ልኮ በጦሩ ውስጥ ከፍተኛ ችግር በመቀስቀሱ እኔ ማብራሪያ እስጣለሁ አንተ አንዳችም ቃል በመሬቱ ዙሪያ እንዳታነሳ በማለት የተማፅኖ መልእክት መላኩን የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ከሁለት ቀን በሁዋላ በምክር ቤት አባሎች ጥያቄ ቀረበ ተብሎ መለስ እራሱ ጥያቄውን አዘጋጅቶ መልሶ መልስ ያለውን ቢሰጥም እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ እራሱ ባዘጋጀው ጥያቄ ግራ ተጋብቶ የተምታታ ምላሽ በመስጠት ለሱዳን መሬት ቆርሶ መስጠቱን በግልጽ በማመኑ በጦሩ ውሰጥ ከፍተኛ ችግር መከሰቱን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

እንደ ምንጮቹ ገለጻ ከሆነ ይሄ እንደሚመጣ ጠርጥረው የነበሩት ወያኔዎቹ ቀኝ እጃቸው የሆነውን ቅልብ የአጋዚ ጦር በቦታው ማስፈራቸውን አስረድተው በአሁኑ ወቅትም ይሄ ጥያቄ በጦሩ ውስጥ ስር በመስደዱ የተደናገጡት እነ መለስ ዜናዊ በቅርቡ ግምገማ በሚል ጦሩን ያነሳሳሉ የተባሉትን መኮንኖችና ወታደሮች ሳይቀር ለመመንጠር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ከኢትዮጵያ መሬት ላይ ቆርሶ ለሱዳን በመሸጡ የተነሳ በጦሩ እና በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ መቀስቀሱን የተረዱት የወያኔ መሪዎች የህዝቡንና የጦሩን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲሉ ብቻ በአዲስ አበባ ከተማ ማክሰኞ ግንቦት 12 ቀን

2000 ዓ.ም የፈንጂ ፍንዳታ አድርሰው 9 ሰዎች ሲሞቱ 4 ሰዎች ደግሞ ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል::

ማክሰኞ ዕለት ከምሽቱ 2:05 ላይ የደረሰው ይኸው የፈንጅ አደጋ ከአራት ኪሎ ወደ ለገሐር በሚጓዝ ታክሲ ላይ የተጠመደ ፈንጅ ፈንድቶ መሆኑ ሲታወቅ በውስጡ አሽከርካሪውን ጨምሮ 14 ሰዎች ጭኖ ሲጓዝ እንደነበረም ታውቋል::

አደጋው የደረሰው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት አቅራቢያ ሲሆን ፍንዳታው እንደ ደረሰ 3 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ የቀሩት በሙሉ ወደ ሆስፒታል ተወስደው የነበረ ቢሆንም ሆስፒታል እንደገቡና በማግስቱ ሌሎቹ 6 ሰዎች ደግሞ ሕይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ ለማወቅ ተችሏል::

የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና የመንግስት ሠራተኞች ያሉበት ከመሆኑም በተጨማሪ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር የነበሩ አንድ የአሜሪካና እስራኤል ጥምር ዜግነት ያላቸው ፕሮፌሰር የዚሁ አደጋ ሰለባ መሆናቸው ሲታወቅ አደጋውን ያደረሰው ቡድን በትክክል አይታወቅም ይባል እንጅ ወያኔ እራሱ የፈጸምው መሆኑን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከሚሰነዘሩት ትችቶች ለማወቅ ተችሎዋል::

አንዳንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እንደሚሉት ከሆነ ሰዓቱን ጠብቆ እንዲህ አይነት ዘግናኝ እልቂት ያደረሰው ወያኔ እራሱ መሆኑን ከዚህ ቀደም በሠራቸው ታሪኮች የምናውቀው በመሆኑ አሁንም በጐንደርና በኑሮ ውድነት የተነሳ ሕዝቡ እያጕረመረመ ባለበት ወቅት የሕዝቡን የትግል አቅጣጫ ለመቀየርና የአሜሪካንን የፀረ ሽብርተኝነት ስሜት ለማጠናከር ሆን ብለው የወሰዱት እርምጃ ነው ሲሉም ይገልፃሉ::

ከዚህ ቀደም በቅርቡ በሼህ አላሙዲ ንብረት በሆነው ኖክ ማደያዎች ላይ ተመሳሳይ ፍንዳታ ደርሶ በርካታ ዜጐች እንደወጡ የቀሩ ሲሆን ዛሬም በሚዘገንን ሁኔታ ፈንጅ በታክሲው ላይ ተጠምዶ እንዲፈነዳ በማድረግ ሌላ ወገን የፈፀመው ለማስመሰል የውጭ ሀገር ዜጐችን ጨምሮ ምሁራን ኢትዮጵያውያን የተሳፈሩበትን ታክሲ ጠብቆ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አጠገብ ድርጊቱ እንዲፈፀም ማድረጉ የሚያሳዝን ነው ሲሉም ገልፀዋል::

ወያኔ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሣራ እየደረሰበት የቆየ ቢሆንም በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እጅግ በሚገርም ሁኔታ በአለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑን የገለፁት እነዚሁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ አገኛለሁ ብሎ ይህንን የመሰለ ዘግናኛ እልቂት በዜጐች ላይ መፈጸሙ አሳዛኝ እና አንገብጋቢ ነው ሲሉ በቁጭት ይገልፃሉ::

ማክሰኞ ግንቦት 12 ቀን በደረሰው የፍንዳታ አደጋ 9ሰዎች መሞታቸው የተረጋገጠ ሲሆን፣ ከተቀሩት ቁስለኞች መካከልም የደከሙ ያሉበት ስለሆነ የሟች ቁጥር ሊጨምር እንደሚችልም ይገመታል::

ወያኔ ከገባበት የፖለቲካ ኪሣራ በተጨማሪ በኢኮኖሚውም ረገድ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ መግባቱን አንዳንድ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ገለፁ::

ሰሞኑን በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የግል ባለሀብቶች ገንዘብ ከባንክ አውጥተው ለመንቀሳቀስ ቢሞክሩም በተለይም ንግድ ባንክ ከ100 ሺ ብር በላይ የለኝም እያለ ሲመልስ እንደነበረም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውስጥ በተንቀሳቃሽ ሂሳብ አስቀምጠው በፈለጉት ጊዜ በመውሰድ ሲጠቀሙ የነበሩት ባለሀብቶች ከ15 ቀን ወዲህ ግን በባንክ ውስጥ ምንም ገንዘብ የለም እየተባሉ ባዶ እጃቸውን እየተመለሱ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ወያኔ ኢኮኖሚውን አሳድጌያለሁ እያለ የተለመደ የውሸት ጡሩንባውንና ቀረርቶውን ቢያሰማም ሀቁ ግን ሀገሪቷ ከድህነት በታች ካሉ ሀገሮች የመጀመሪያ ተርታ ተሰልፋ የምትገኝ መሆኑን የገለፁት የኢኮኖሚ ባለሙያዎች የኢኮኖሚ እድገት የፖለቲካ ጨዋታ አይደለም በተግባር ሰርቶ ውጤት ማሳየት ሲቻል ነው አሁን እነ ወያኔ የሚሉት ግን ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ሆኖ እየታየ ያለ ሐቅ ነው ሲሉም ተችተዋል::

በቅርቡ በተለይ ከ15 ቀናት ወዲህ በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ እንደሌለ ብሔራዊ ባንክ ለግል ባለሀብቶች የገለፀላቸው መሆኑን ያስረዱት እነዚሁ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት በሀገሪቱ ውስጥ የውጭ ገንዘብ የሌለ በመሆኑ ለመመንዘር እንደተቸገሩና ከ3ወር በኋላ ተመለሱ ተብለው እንደተነገራቸው ያስረዱ ሲሆን የንግድ ስራ ቆይ ለበሁዋላ ተብሎ አይሰራም እናም ለከፍተኛ ኪሣራ ተዳርገናል በዚህ ላይ አመታዊ ግብር ሲመጣ ያልሰራንበት ሁሉ ተደምሮ አናታችን ላይ ይቆለላል:: ምን ማድረግ እንደሚገባን ቸግሮናል ሲሉም በምሬት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የውጭ ገንዘብ ምንዛሬ የለም ብሎ ብሔራዊ ባንክ ለንግዱ ሕብረተሰብ ምላሽ በሰጠ በማግስቱ የሀገር ውስጥ ገንዘብም የለም ከ100 ሺ ብር በላይ ከባንክ ማውጣት አትችሉም እያለ ንግድ ባንክ ምላሽ መስጠቱ ወያኔ የኪሣራዎች ኪሣራ እየደረሰበት መሆኑን የሚያስረዳ ምልክት ነው ያሉት የንግዱ ሕብረተሰብ አባላት የወያኔ ባለስልጣናት የውጭ ገንዘብ ይገኝባቸዋል ብለው የጠረጠሩዋቸውን የቡቲክና ሌሎችም ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩትን ንፁሀን ዜጎች የውጭ ገንዘብ

ስትመነዝር ተገኝተሀል እያሉ በሀሰት በሱቅ ውስጥ የተገኘውን የውጭ ሀገር ብር እንደዘረፏቸውና 45 ያህል ነጋዴዎችንም አፍሰው ለእስር እንደዳረጓቸው ታውቋል::

ዛሬ ሀገሪቷ በችግር ውስጥ ተዘፍቃ የአለም ምግብ ደርጅት አስቸኳዋይ እርዳታ ለአትዮጵያውያኖች ይሰጣቸው እያለ በሚወተውትበት ወቅት የወያኔ ቡድን ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በሀገሪቱ ችግር እንደሌለ አስመስሎ ቢያቅራራም እውነትና ንጋት እያደር ይወጣል እንዲሉ ሀቁ ወጥቶ የአለም ማህበረሰብ እየወተወተ ይገኛል::

10 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግቢያለሁ እያለ ሲወተውት የሰነበተው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊና ቡድኑ እውነታውን እያወቁት የአለም አቀፍ ተቋማትን ለማታለል ቢዳክሩም እነሱ ቀድመው በማወቃቸው ቡድኑ ከፍተኛ የፖለቲካና የአኮኖሚ ኪሳራ ውስጥ መዘፈቁን እንደ ደረሱበት የዲፕሎማቲክ ምንጮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየገለፁ ይገኛሉ::

በቅርቡ በባንክ ዙሪያ ባወጣው አዲስ አዋጅ መሰረት ማንኛውም የግል ባንክ ከተቀማጭ ገንዘባቸው ላይ 20 በመቶ በብሔራዊ ባንክ ተቀማጭ ማድረግ አለባቸው የሚል መመሪያ አውጥቶ ገንዘቡ ሁሉ በወያኔ ካዝና ውስጥ የገባ ሲሆን፣ እንዲህም ሆኖ ለንግዱ ሕብረተሰብ ገንዘብ የለም እያሉ እየመለሷቸው መገኘቱ አሳዛኝ ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው::

ወያኔ ከገባበት የፖለቲካ ኪሣራ ለማገገም ሲል ብቻ በወታደራዊ ኃይል እየተጠቀመ ቢሆንም ውጤቱ በየቀኑ ቁልቁል እያሽቆለቆለ መሆኑና ውጤት አልባ ሆኖ እየታየ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ለወታደራዊ ቁሳቁሶች መግዣ እያዋለው የንግዱን ሕብረተሰብ በችግርና በኪሣራ የዳረጋቸው መሆኑ እየተዘገበ ይገኛል::

የወያኔው ቡድን የሚያደርገው አጥቶ እንደ አበደ ውሻ እየተቅበዘበዘ ባለበት በዚህ ወቅት የመዋቅር ለውጥ በሚል በርካታ የመንግስት ሠራተኞችን ለማባረር ባቆበቆበበት ወቅት አንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ማፍረሱ ታወቀ::

ከፍተኛ ገንዘብ የሚሰበስበው የገቢዎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የተባለውን ያፈረሰው ሲሆን በውስጡ ያሉ ሠራተኞችም ለጊዜው ባሉበት እንዲቀጥሉ ቢባልም ያለው ሁኔታ ግን በቀጣይነት የሚያስኬድ ባለመሆኑ በርካታ ሰራተኞችን እንደሚያባርር ከወዲሁ የብዙዎችን ስጋት አሳድሮዋል::

የገቢዎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን አፍርሶ በጉምሩክ ባለሥልጣን ስር የተካተተ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ከፍተኛ ገንዘብ ሲሰበስብ የነበረውን መስሪያ

ቤት  አፍርሶ  ወደ  መምሪያ  ዝቅ ከማድረጉም ባሻገር የጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት  የያዘውን በአግባቡ ያልተወጣ  አሁን ደግሞ ይበልጥ  ለንግዱ ሕብረተሰብ ችግሩን ውስብስብ ለማድረግ ይህን የመሰለ ስራ መሠራቱ እንዳሳዘናቸውም እነዚሁ ወገኖች  በምሬት ሲገልፁ  ተደምጠል፡፡

የገቢዎች  ሚኒስቴር  ሚኒስትር  የብአዴኑ ሰው  መላኩ ፈንታ  የነበረ ሲሆን፣  ከወርቅ መጭበርበር  ጋር በተያያዘ ለፖሊስ  ቃሉን የሰጠ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ይህ በተከሰተ  በቅርብ  ቀናት  ውስጥ ሚኒስቴር መስሪያ  ቤቱ  ፈርሶ እሱም ወደ  አዲስ  አበባ ከተማ  መስተዳድር ቢሮ ውስጥ  እንዲገባ መደረጉን ምንጮቹ  ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ  ዜና  የአዲስ አበባ  ከተማ ከንቲባ አቶ  ኩማ ደመቅሳ የተባለው ሆድ አደር ምርኮኛ መሾሙ ታወቀ ፡፡  ማክሰኞ  ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም  በተደረገው በዚሁ ሹመት ላይ  ኩማ  ደመቅሳ  ከንቲባ ሲሆን የብአዴኑ ከፍያለው አዘዘ  ደግሞ ምክትል ከንቲባ  ሆኖ  ተሹሟል፡፡

ሲመራው የነበረው  የገቢዎች  ሚኒስቴር መስሪያ ቤት  የፈረሰበት  መላኩ ፈንታ በምክትል ከንቲባነት  እንደሚሾም  ተወስኖ የነበረ  ቢሆንም ጉዳዩ ባልታወቀ ምክንያት  ተቀይሮ  ሌላው  የወያኔ ካድሬ  መተካቱ  ታውቋል፡፡

በረሀ በምርኮኛነት የውሀ ጀሪካን ሲያመላልስ የነረበው ኩማ ደመቅሳ በ1981 ዓ.ም. ደራ ላይ ኦ.ህ.ዴ.ድ.የተባለው የወያኔ ጀሌ ድርጅት ሲመሰረት ለዚህ ድርጅት ማሙያ እንዲሆኑ ከተሰበሰቡት ምርኮኞች መካከል አንዱ ሲሆን ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝደንት ሆኖ በህወሃት ክፍፍል ወቅት ከአንጃው ጋር ንክኪ አለው ተብሎ ከስልጣኑ ተባርሮ ቆይቶ የነበረና በሁዋላም የብሄር ስብጥር ለማሙያ ሲባል የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ ተሹሞ እንደ ነበር የገለጹት  ለግለሰቡ ቅርበት ያላቸው ወገኖች በአሁኑ ወቅት ደግሞ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆኖ ተሸሞዋል፡፡

ምንም እንኩዋን ኩማ ከንቲባ ሆኖ የተሾመ ቢሆንም በስውር የበላይ ተቆጣጣሪው የብአዴኑ ሕላዊ ዮሴፍ መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልጸዋል፡፡

በአሁን ወቅት የመከላከያ ሚኒስትር በቦታው የሌለ በመሆኑ በቅርቡ እንደሚሾም ምንጮቹ ጠቁመው ቦታው የኦህዴድ በመሆኑ ማንን ለመሾም እንደተዘጋጁ ባይታወቅም ለቦታው ይመጥናል ሳይሆን ማን ይታመናል የሚለው ለነመለስ ትልቅ የራስ ምታት እንደሆነባቸውም ምንጮቹ ሳይገልጹ አላለፉም፡፡